የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

# ፓርላማ ዜና መጽሔት

6ኛው የኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ5ኛ አመት የስራ ዘመኑ ታህሳስ 21 እና 23 ቀን 2018 ዓ.ም በአካሄዳቸው መደበኛ ስብሰባዎች የኢፌዲሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር እና የፍትሕ ሚኒስቴር ሚኒስቴር በምክር ቤቱ በመገኘት ከምክር ቤት አበላት ለቀረበላቸው ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

በዚህ ወር ምክር ቤቱ የተለያዩ ረቂቅ አዋጆችን መርምሮ ያጸደቀ ሲሆን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ዕጩ ዳኞችና የመገናኛ ብዙኃን ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተርን ሹመት አጽድቋል፡፡

የታህሳስ ወር ዜና መጽሔታችን እነዚህንና ሌሎችን አበይት ምክር ቤታዊ ጉዳዮች ታስነብባለች፡፡

ዓበይት ርዕሶች
ህግ አወጣጥ
ክትትል ቁጥጥር
ሹመት

መልካም ንባብ!
ታህሳስ፣ 2018ዓ.ም

## ህግ አወጣጥ

### የኢ.ፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ5ኛ ዓመት የሥራ ዘመኑ ታህሳስ 14 ቀን 2018ዓ.ም በአካሄደው 5ኛ መደበኛ ስብሰባ የእፅዋት ጥበቃ እና ኳራንታይን ረቂቅ አዋጅን መርምሮ አፅድቋል::



የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ አቶ ሰለሞን ላሌ ረቂቅ አዋጁን አስመልክቶ ቋሚ ኮሚቴው ያዘጋጀውን ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ በአቀረቡበት ወቅት ረቂቅ አዋጁ ከጊዜ ወደ ጊዜ በፍጥነት እየተሻሻሉና እየተለወጡ የመጡትን ዓለም አቀፋዊ የእፅዋት ጥበቃ እና ኳራንቲን ደረጃዎችና አሰራሮች በመከተል ከዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ጋር የተናበበ ቀልጣፋ እና ውጤታማ ሥራ ለመስራት መደላድል ይፈጥራል ብለዋል፡፡

አግባብነት ያለውና ደረጃውን የጠበቀ የተባይ አሰሳና ቅኝት ሥጋት ትንተና ለማድረግ እና በመግቢያ በሮች የገቢና ወጪ እፅዋት፣ የእፅዋት ውጤት እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቁሶችንበተገቢው ለመቆጣጠር

የሚያስችልማዕቀፍያለውመሆኑንእንዲሁምዘመናዊ የተባይ መከላከል እና መቆጣጠር ሥርዓትን በመዘርጋት ምርታማነትንና የምርት ጥራትን በማሳደግ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ተጠቃሚነት በማረጋገጥ ረገድ ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለውም ለምክር ቤቱ አስረድተዋል፡፡

ምክር ቤቱ በረቂቅ አዋጁ ላይ ሰፊ ውይይት ካደረገ በኋላ የእፅዋት ጥበቃ እና ኳራንታይን ረቂቅ አዋጅን አዋጅ ቁጥር 1400/ 2018 በማድረግ በሙሉ ድምጽ አፅድቆታል።

በተያያዘ ዜና ምክር ቤቱ በ5ኛ ዓመት የሥራ ዘመኑ ታህሳስ 21 ቀን 2018 ዓ.ም በአካሄደው 6ኛ መደበኛ ስብሰባ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ረቂቅ አዋጅን መርምሮ አጽድቋል፡፡




ረቂቅ አዋጁ በዋናነት ለውሃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ እንዲሁም በተባባሪነት ለፕላን፣ በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የተመራ ሲሆን ቋሚ ኮሚቴዎቹ በጋራ ያዘጋጁትን ሪፖርትና የውሳኔ ሀሳብ

የውሃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ ፈቲያ አህመድ ለምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡

ረቂቅ አዋጁ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች ለኢኮኖሚ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ በፖሊሲዎችና በውሳኔ አሰጣጥ ላይ እየተንጸባረቀ የሚገኝ መሆኑን የተከበሩ ወ/ሮ ፈቲያ አህመድ ገልጸዋል።

የሥርዓተ ምህዳርን በዘላቂነት ለማስተዳደር የሚያስችል የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ የሕግ ማዕቀፍ እና የአሠራር ስርዓቶችን መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ የተዘጋጀ ረቂቅ አዋጅ መሆኑን የተከበሩ ወ/ሮ ፈቲያ ለምክር ቤቱ አስረድተዋል፡፡

ምክር ቤቱ በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ረቂቅ አዋጅን አዋጅ ቁጥር 1401/2018 አድርጎ በአንድ ድምፅ ተአቅቦ በአብላጫ ድምጽ አጽድቋል፡፡



## ክትትል ቁጥጥር

ምክር ቤቱ በ5ኛ ዓመት የሥራ ዘመኑ ታህሳስ 07 ቀን 2018 ዓ.ም በአካሄደው 4ኛ መደበኛ ስብሰባው የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር ሚኒስትር ክቡር አለሙ ስሜ (ዶ/ር) ከምክር ቤት አባላት ለቀረበላቸው ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡





ህገወጥ ኬላዎችን፣ የአየር መንገዶችን የግንባታ አፈጻጸም፣ የትረፊክ አደጋን፣ የትራንስፖርት ዘርፉን ከማዘመን አንጻር በአጠቃላይ በትራንስፖርት ዘርፉ ከሚስተዋሉ ችግሮች እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች የተመለከቱ ጥያቄዎች በምክር ቤቱ አባላት ለትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ሚኒስትር ክቡር አለሙ ስሜ (ዶ/ር) ቀርበዋል፡፡

ሚኒስትሩ በትራንስፖርት ዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍ ዘርፉን ለማዘመን በትኩረት እየተሰራ መሆኑን አብራርተዋል።ህገወጥ ኬላዎች በሀገር ኢኮኖሚ እድገት ላይ የሚያሳድሩት አሉታዊ ተጽዕኖ በአግባቡ ተገምግመው ቁጥጥር እተደረገባቸው በመሆኑ ቁጥራቸው እየቀነሰ መምጣቱን

የገለጹት አለሙ ስሜ (ዶ/ር) በቀጣይም ህገወጥ ኬላዎችን የማስወገድ ስራው ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል ብለዋል፡፡

በሀገሪቱ የተለያዩ ክልሎች የአየር ማረፊያዎች ግንባታቸው የተጀመረው በክልል መንግሥታት እና በባለሀብቶች መሆኑን ገልጸው ግንባታቸው ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የቴክኒክ ድጋፍ እንደሚያደርግ እና የግንባታ ሂደታቸው የመጓተት ችግር የሚስተዋልባቸውን የአየር ማረፊያዎች ችግሩ መፍትሔ እንዲያገኝ ርብርብ እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

ክቡር አለሙ ስሜ (ዶ/ር) የትራፊክ አደጋን ለመቀነስ ለአሽከርካሪዎች ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና እየተሰጠ መሆኑን ገልጸው አዲሱ የተሽከርካሪ ሰሌዳ ታርጋ እየተለየ የሚፈጸመውን አድሎአዊ አሰራርን ጨምሮ በርካታ ችግሮችን የሚፈታ ነው ሲሉ ለምክር ቤቱ አብራርተዋል፡፡

በትራንስፖርት ዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍ እና የአሠራር ስርዓቱን ለማዘመን በትኩረት እየተሰራ መሆኑን የገለጹት ክቡር ሚኒስትሩ የተሽከርካሪዎችን ሰሌዳ ቀይሮ ዲጂታላይዝ የማድረግ ሥራው በቅርቡ ተጠናቆ የሚሰራጭ መሆኑን ተናግረዋል።

**በሌላ በኩል ምክር ቤቱ በ5ኛ ዓመት የሥራ ዘመኑ ታህሳስ 21 ቀን 2018 ዓ.ም በአካሄደው 6ኛ መደበኛ ስብሰባ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ክቡር ጌዲዮን ጢሞቲዎስ (ዶ/ር) ከምክር ቤት አባላት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡**





በዕለቱ በተካሄደው ጉባኤ በምክር ቤቱ አባላት በፐብሊክ ዲፕሎማሲ፣ በቆንስላ ጽ/ቤት አገልግሎት ተደራሽነት፣ ሀገራችን ከጎረቤት ሃገራት ጋር ስላላት ግንኙነት፣ ከባህር በር ተጠቃሚነት አንጻር፣ በውጭ ሃገራት የሥራ ሥምሪት እና የዜጎችን ደህንነት ማስጠበቅን የተመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡



ክቡር ጌዲዮን ጢሞቲዎስ (ዶ/ር) ከምክር ቤት አባላት ለቀረበላቸው ጥያቄ ምላሽ ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት ኢትዮጵያ ያቀረበችው የባህር በር ጥያቄ የመንግሥት ወይም የአንድ ፓርቲ ጥያቄ ብቻ ሳይሆን ትውልድ ተሻጋሪ ግብ ያለው የትውልድ ጥያቄ ነው ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያን የባሕር በር ባለቤትነት ለማረጋገጥ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን ጨምሮ የተለያዩ ኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ከፍተኛ ሥራ እያከናወኑ መሆኑን የገለጹት ሚኒስትሩ በተለያዩ ሀገራት የሚገኙ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችም የሀገሪቱን የባሕር በር ፍላጎት ለማሳካት እያከናወኑት ያለው ተግባር አበረታች እንደሆነም ገልጸዋል።

በቀጣይም የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ለማስከበር በሚደረገው ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ሁሉም ዜጋ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት ሊወጣ ይገባልም ብለዋል፡፡

ከፐብሊክ ዲፕሎማሲ አንጻር ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመሆን ኪን ኢትዮጵያን በማዘጋጀት በተለያዩ ሃገራት በመሄድ የኢትዮጵያን ባህል የማሳየት ሥራ መሠራቱን አብራርተው በኢትዮጵያ እየተሠሩ ያሉ የልማት ሥራዎችን ትላልቅ ጋዜጠኞችን በማስጎብኘት እንዲሁም በዲጂታሉ መስክ ተጽዕኖ ፈጣሪ የሆኑ የማህበራዊ ሚዲያ አንቂዎች ለኢትዮጵያ ድምጽ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ሕዝብ ለሕዝብ ሥራዎች ተሰርተዋል ብለዋል፡፡

የቆንጽላ ጽህፈት ቤት አገልግሎትን በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ተደራሽ ለማድረግ በቴክኖሎጂ በመታገዝ ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት ጥረት እየተደረገ መሆኑንም ክቡር ሚኒስትሩ ገልጸዋል፡

አክለውም ከተለያዩ አገራት ጋር የሥራ ሥምሪት ስምምነቶች በማድረግ በሕጋዊ መንገድ የውጭ ሃገራት ሥራ ሥምሪት እየተደረገ በውጭ ሃገራት ለሥራ የተሰማሩት ዜጎች ችግር ሲያጋጥማቸው በኤምባሲዎች፣ በቆንስላ ጄኔራሎች እንዲሁም ሚሲዮኖች መብታቸው እንዲከበር ክትትል የማድረግ ስራዎች እየተሰሩ ነው ብለዋል፡፡

እንደ ሃገር የህዳሴ ግድብ ግንባታ መጠናቀቅ መቻሉ ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያላትን ጠንካራ ግንኙነት ማሳያ እንደሆነ ገልጸው ችግሮች ሰፈጠሩ ንግግርና ውይይት በማድረግ ከጎረቤት ሃገራት ጋር ጠንካራ ግንኙነት እንዲኖር ሥራዎች እየተሰሩ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

በተያያዘ ዜና ምክር ቤቱ በ5ኛ ዓመት የሥራ ዘመኑ ታህሳስ 23 ቀን 2018 ዓ.ም በአካሄደው 7ኛ መደበኛ ስብሰባ የኢፌዲሪ የፍትሕ ሚኒስቴር ሚኒስትር ክብርት ሐና አርያሥላሴ ከምክር ቤት አባላት ለቀረበላቸው ጥያቄዎች በምላሽና ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡








የዜጎችን ዲሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብት ከማስጠበቅ፣ ከፍትሕ አገልገሎት አሰጣጥና ተደራሽነት አንጻር እንዲሁም ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን የተመለከቱ ጥያቄዎች በምክር ቤት አባላት ቀርበዋል፡፡

ክብርት ሃና በማብራሪያቸው ማንኛውም አካል የመብት ጥያቄ ሲኖረው ሕገ መንግሥቱን እና የሀገሪቷን ሕጎችን ባከበረ መንገድ ሊያቀርብ እንደሚገባ አስገንዝበው ከሕግ ውጭ የሆኑ ጉዳዮች ሲኖሩ ግን በየደረጃው ተጠያቂነት የሚረጋገጥበት ሥርዓት አለ ሲሉ ገልጸዋል፡፡

አክለውም የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥና የዜጎን መብቶች ለማስጠበቅ በየደረጃው የሪፎርም ሥራዎች መተግበራቸውን አንስተው ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አስፈላጊ የለውጥ ሥራዎችን በትኩረት እየሠራ ነው ብለዋል፡፡

ከፍትሕ አገልግሎት አሰጣጥና ከወንጀል ጋር በተገናኘ ለተነሱ የአገልግሎት አሰጣጥ ጥያቄዎች የወንጀል ጉዳዮች በባህሪያቸው ውስብሰብነት ያላቸው እና ዝርዝር መረጃና ማጣራትን የሚፈልጉ በመሆናቸው ጊዜ ሊወስዱ የሚችሉ መሆኑን ጠቁመው የወንጀል እና የፍትሕ ጉዳዮች ዝርዝር መረጃ ማጣራትን እንደሚጠይቅና የማጣራቱ ሥራ ጊዜ ተወስዶ በጥንቃቄ የሚሰራ መሆኑን ከግምት ውስጥ ማስገባት ተገቢ ነው ሲሉ ክብርት ሃና አርያስላሴ አብራርተዋል፡፡

## ሹመት

ምክር ቤቱ ታህሳስ 28 ቀን 2018 ዓ.ም በአካሄደው 8ኛ መደበኛ ስብሰባው የተለያዩ ሹመቶችን መርምሮ አጽድቋል፡፡

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር እና 34 የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ዕጩ ዳኞች ሹመት መርምሮ አጽድቋል።

በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግስት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር የተከበሩ ተስፋዬ በልጅጌ (ዶ/ር ) የሹመቶቹን የውሳኔ ሀሳቦች አቅርበዋል።



ምክር ቤቱ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ መርምሮ ክብርት ወ/ሮ ሃይማኖት ዘለቀ ወርቅነህ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አድርጎ የውሳኔ ቁጥር 3/2018 በማድረግ በሙሉ ድምጽ አጽድቋል።





በተያያዘ ምክር ቤቱ 34 የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ዕጩ ዳኞች ሹመትን የውሳኔ ሃሳብ ቁጥር 4/2018 አድርጎ በአንድ ድምጸ ተአቅቦ በአብላጫ ድምጽ የጸደቀ ሲሆን ተሿሚዎቹ በምክር ቤቱ ፊት ቀርበው በታማኝነት እና በቅንነት ለማገልገል ቃለ-መሀላ ፈጽመዋል።




ለበለጠ መረጃና አስተያየት
አድራሻ (Address)
ስልክ Tel:- 011-154-52-33
ነፃ ስልክ ጥሪ Free call 8557
ፖስታ ሳጥን ቁጥር P.O.Box : 80001
ኢ..ሜይል E-mail info@hopr.gov.et


በኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽ/ቤት የኮሙኒኬሽን፣ አስተህምሮና ሙዚየም መሪ ሥራ አስፈፃሚ የተዘጋጀ፣